**አባ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ**
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአኵሱም፣
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣
የዓለም ሃይማኖቶች ምክር ቤት
ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት

**ABBA PAULOS I**
Patriarch of Ethiopia, Archbishop of Axum,
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot,
President of WCC and Honorary President of
World Religions for Peace


ቁጥር ____________________
Ref. No.

ቀን ______________________ ዓ.ም
Date

መዋቅሮችን እየጣሰ የመሥራት ተልእኮውን እንደቀጠለ መሆኑ ከቀረበልን ሪፖርትና የጽሑፍ ሠነድ መረዳት አስችሎናል።

ይህ የአሠራር ቸልተኛነት ሊደርስ የቻለው ውሳኔዎችን የመፈጸምና የማስፈጸም ሥልጣን የተሰጠው ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት መሆኑ እየታወቀ ጽሕፈት ቤቱ እንደ ጉዳዩ ክብደት በቅደም ተከተል ደረጃውን በጠበቀ መንገድ ትኩረት ሰጥቶ ከበላይ አካል የተላለፈውን ውሳኔ መፈጸምና ማስፈጸም ሲገባው ይህን ባለማድረጉ የኃላፊነት ድርሻውን ያልተወጣ ስለሆነ ሊወቀስ ይገባዋል።

አሁንም ውሳኔ ባገኙ ጉዳዮች አፈጻጸም ዙሪያ እየታየ ያለውን የሥራ ድክመት ማስወገድ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ አመራር መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ ተገድደናል።

ስለዚህ፡-

1. የመንግሥት አካላትና የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ፣ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ በተገኙበት የተላለፈው የጋራ ውሳኔ በሥራ ሳይተረጎም የቀረበት ምክንያት በአጭር ጊዜ ውስጥ በአስተዳደር ጉባኤ ተመርምሮ ውሳኔው ተፋጥኖ እንዲደርሰን፤
2. ይህ ደብዳቤ ከደረሳችሁ ጊዜ ጀምሮ ውሳኔው ሥራ ላይ ይውል ዘንድ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በኩል ለሁሉችም አህጉረ ስብከትና ለሚመለከታቸው ሁሉ በአስቸኳይ እንዲተላለፍ፤
3. በአስተዳደር ጉባኤ መመርመር የሚገባቸውን ሠነዶች በተመለከተ መስከረም 12 ቀን 2002 ዓ.ም የተላለፈውን ውሳኔ ጨምሮ ከሰንበት ትምህርት ቤቶች ማዳጃ መምሪያ በየጊዜው የቀረበውንና ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ጽሑፎች በድምሩ
4. 50 ገጽ ፎቶ ኮፒ በዚህ ደብዳቤ ሸኝነት እንዲደርሳችሁ ያደረግን መሆኑን እናስታውቃለን።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ

ABBA PAULOS (Dr.)
Patriarch of Ethiopia,
Archbishop of Axum
Echegue of the See of St. Tekle Haimanot.
President of WCC and
Honorary President of World Religions Conference for Peace

<u>ግልባጭ ፡-</u>
- ለቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
- ለፌደራል ጉዳዮች መምሪያ
- ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ

<u>አዲስ አበባ</u>


☎ 251-111-111989, 251-111-550577, 251-111-565747, 251-111-551013
Fax፡- 251-111-552211
✉ 1283 **አዲስ አበባ** Addis Ababa
E-mail: aba.paulos.patriarch@ethionet.et
abagerima@yaho.com